የሰ/መ/ቁ. 39601

ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - አክሊሉ ተስፋዬ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ገዛኸኝ መንግስቱ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በመዝገቡ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ለንግድ የሚውሉ እህሎችን ይዞ የነበረው መጋዘን በመታሸጉ ምክንያት ደርሶአል የተባለውን ጉዳት(ኪሣራ) ለማስከፈል በሚል የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ የተለያዩ እህሎችን ሲነግድበት የነበረው የንግድ ቤት መጋዘን ከሕግ ውጪ አሽጐ ሁከት የፈጠረበት መሆኑን፣በዚህ ምክንያትም ሁከቱ ይወገድለት ዘንድ በፍ/ቤት ክስ መመስረቱን፣አመልካች ለክሱ መልስ እንዲሰጥ ታዞ መቅረቡና ክርክር መደረጉን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ሁከቱ ይወገድ ሲል በመወሰኑ መጋዘኑ መከፈቱን በአንድ በኩል ሲገልጽ፤በሌላ በኩል ደግሞ የቀረበው ክስ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ መጋዘኑ ለአራት ወር ያህል ተዘግቶ በመቆየቱ ምክንያት በእህል ዋጋ ረገድ ደረሰ የተባለው ኪሣራ ብር 9,959(ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ) እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ተጠሪ የጠየቀውም ይኸው ብር 9,959(ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ) ከወለድና የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፈለው እንዲወሰንለት ሲሆን፣ፍ/ቤቱም በጥያቄው መሰረት ወስኖለታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረም ዘንድ አቤቱታ አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ክርክሩን አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ተጠሪ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ክስ የመሰረተው ሁለት ጊዜ ነው፡፡ የመጀመሪያው ከሕግ ውጪ ተደረገ የተባለውን እሽግ እንዲነሳለት የሚጠይቅ ሲሆን፣ሁለተኛው ደግሞ መጋዘኑ በመታሸጉ ምክንያት ደረሰ ያለውን ኪሣራ እንዲከፈል የሚጠይቅ ነው፡፡ የኪሣራው መጠን ያሰላው የእሕሉን የመሸጫ ዋጋ ነው(ነበር) ያለውን መሰረት በማድረግ እንደሆነም በክሱ ተመልክቶአል፡፡ አመልካች በበኩሉ በሁለተኛው ክስ የተጠየቀው ኪሣራ በመጀመሪያው ክስ ሊጠየቅ ይገባው የነበረ በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ኪሣራው በእርግጥ ለመድረሱ ማስረጃ አልቀረበም የሚል የፍሬ ነገር ነጥብ በማንሳት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱ ሁለቱንም የመከራከሪያ ነጥቦች አልተቀበለም፡፡

ክሱን ያስተናገደው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዳየነው ተጠሪ በመጋዘኑ መታሸግ ምክንያት በእህሉ ላይ የደረሰውን ብልሽት ወይም ኪሣራ የሚያሳይ ማስረጃ እንዳላቀረበ ፍ/ቤቱ ስለመገንዘቡ በውሳኔው ላይ በግልጽ አመልክቶአል፡፡ "... ከሣሽ ከተለየ የእህል ንግድ ላይ ያጣውን የገንዘብ መጠን አሚልቶ በዚህ ላይ መዘረዘሩ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ ይህንን ያሕል ገቢ ለማግኘቱም ሆነ ለማጣራቱ የተመሰከረ ነገረ የለም፡፡ ይህንን የራሱን ገቢ ተከሣሽ በክርክሩ ላይ እንደተቃወመው የተመዘገበ የገቢ ግብር የተከፈለበት ለመሆኑ ማስረጃ የለም.." በማለትም በውሳኔ ሐተታው ላይ ተችቶአል፡፡ የደረሰበት መደምደሚያ ይህ እንደሆነ ከገለጸ በኋላም ነው ተጠሪ ካሣ(ኪሣራ) ይገባዋል በማለት ገንዘብ እንዲከፈል የወሰነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ፍ/ቤቱ በተጠሪ ላይ ኪሣራ ለመድረሱ ምንም አይነት ማረጋገጫ አላገኘም፡፡ ይህንንም እንዳመነበት በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ ገንዘቡ መከፈል አለበት ለማለት የቻለው በእርግጥም ኪሣራው ስለመድረሱ በተጨባጭ ማስረጃ አረጋግጦ ሳይሆን፣መጋዘኑ ታሽጐ ከቆየ ተጠሪ ያጣው ማስረጃ አረጋግጦ ሳይሆን፣መጋዘኑ ታሽጐ ከቆየ ተጠሪ ያጣው ነገር የለም ለማለት አይቻልም ከሚል ግምት በመነሳት እንደሆነ በውሳኔው ማጠቃለያ ላይ በግልጽ አመልክቶአል፡፡ ኪሣራ ሊከፈል የሚችለው ጉዳት ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2090 እና 2091 ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን የደረሰ ጉዳት ለመኖሩ በምንም አይነት መንገድ አልተረጋገጠም፡፡ በመሆኑም ክሱ ለሁለተኛ ጊዜ እንደቀረበ ይቆጠራል ከሚል መነሻ አመልካች አቀርቦት የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቢታለፍ እንኳ በክርክሩ ፍሬ ነገር ተገብቶ የደረሰ ጉዳት አለ ለማለት የሚያስችል የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት ስለሌለ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07105 ኀዳር 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47571 ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ኪሣራ የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ